# ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በኮለምበስ ፤ ኦሃዮ

ወያኔ/ኢሕአዴግ ከሱዳን ጋር የምስጢር ስምምነት በማድረግ ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር ጎኑ ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሜትር የሚደርሰውን የምዕራብ ኢትዮጵያ ወሃ-ገብ ለም መሬትና ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ያለውን ድንበራችንን በገጸ በረከትነት ለሱዳን መስጠቱ የሚታወቅ ነው። የሱዳን ጦርም ወረራ አካሂዶ በወገኖቻችን ላይ ግድያ ፣ አፈናና ከፍተኛ መፈናቀል ፤ እንዲሁም በንብረት ላይ ዘረፋና ቃጠሎ አድርሷል። በዚህም ሳቢያ ፣ የአካባቢው ወገኖቻችን ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር በታላቅ ትግል ላይ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት ሰፍኖ ይገኛል።

በዚህ አኳያ ፣ ዳር ድንበራችንን ታሪካዊ ሁኔታ በተመለከተ ፤ በአካባቢው የሚካሄደውን ከፍተኛ የሕዝብ መፈናቀል ፤ በእናት ሃገራችን ላይ የሚፈጸመውን ወደር የሌለው ክህደት ፤ የወደፊት ተጠያቂነት ፤ ሰብዓዊና ሲቪል መብቶች ጥሰትና ኢትዮጵያዊነትን በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያና ግንዛቤ እንዲሰጡን 2 ታላላቅ ኢትዮጵያውያንን ጋብዘናል። እነርሱም ፥

1ኛ/ ዶ/ር ዳንኤል ክንዴ - በአፍሪካ ቀንድና በመካከለኛው ምሥራቅ የታሪክ ፣ የፖለቲካ ሣይንስና የኢኮኖሚ ሊቅ

2ኛ/ አቶ ኦባንግ ሜቶ - የሰብዓዊ መብቶች ታጋይና የአኝዋክ ፍትህ ካውንስል መስራችና መሪ

ስለዚህ በኮለምበስ ከተማና አካባቢው ፣ በሲንሰናቲ ፣ በክሊቭላንድና በዴይተን ከተማዎች ፤ እንዲሁም በአጎራባች ስቴቶች - ሚሽጋን ፣ ኢንዲያና ፣ ኬንታኪ ፣ ዌስት ቨርጂኒያ እና ፔንሰልቫኒያ - የምትኖሩ ሃገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ እንድትገኙ ከታላቅ አክብሮት ጋር ጠርተናችኋል።

**ቀን - SATURDAY, AUGUST 23, 2008**

**ሰዓት - 2:00 PM - 6:00 PM**

**ቦታ - Ramada East-Airport**
**4801 East Broad Street**
**Columbus, OH 43213**
**@ the corner of East Broad Street**
**and South Hamilton Road**




**ለተጨማሪ መረጃ - 614.354.9515**

**የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**